# ኢትዮጵያና ኤርትራ ከየት ወደየት?

ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ

በሁለተኛው የኢትዮጵያና የኤርትራ ወዳጅነት ጉባኤ
ሳንሆዜ, ካሊፎርኒያ ግዛት, መጋቢት 3 – 5, 2002
ከቀረበው ጽሑፍ የተወሰደ

ክቡር ሊቀመንበር!

ክቡራትና ክቡራን!

ከሁሉ አስቀድሜ ይህ ስብሰባ ይሳካ ዘንድ በምክርና በገንዘብም በኩል ዕርዳታ ያደረጉትን ኢትዮጵያውያንን እና ኤርትራውያንን ከልብ እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ።

በመጀመሪያ ደረጃ ያሉት፤ አበበ ገላጋይ፣ ሃጎስ ተክሌ፣ ጌታቸው ረዳ፣ ፈቃደ አደራ፣ ዘሪሁን ሽፋ፣ ጌታሁን ኃይሉ፣ መክብብ ሲያምረኝ፣ አያልነህ ውባለም ሲሆኑ ፣ እንዲሁም ዶክተር ወርቁ ነጋሽ፣ ኢንጅነር ቴዎድሮስ አንለይ፣ ማሩ አራጋው፣ ዶክተር ደምሴ አሉማ፣ ብንያም ሙሉጌታ፣ ደምሴ ደዬ፣ ሁሴን ዓለሙ፣ ላቀው መለሰ እና ከሰተ አያልነህ ይገኙበታል።

የስብሰባው ዓላማ ምን ነበር? ቢባል የአጭር ጊዜ ዓላማው፦ የኢትዮጵያንና የኤርትራን ሕዝብ አሞች በሆነ መንገድ ሁሉ ለማቀራረብ ሲሆን፣ የረጂም ጊዜ እቅዱ ደግሞ ሁለቱ አገሮች በእኩልነት፣ በመግባባትና በመተባበር አንድ ሆነው የሚኖሩበትን መንገድ ለመወያየት ነው።

ማቀራረቡ ለምን አስፈለገ? ተብሎ ቢጠየቅ ብዙ የሆነ መልስ ለመስጠት ይቻላል። ባጭሩ ግን ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ተጣልተው በሕዝብ ደረጃ የተዋጉበት ጊዜ ኑሮ አያውቅም። ሆኖም ተዋጊዎቹ ሕዝቡ ጭቆና ስለበዛበት ኤርትራን ነጻ እናውጣ ብለው ሲታገሉ፣ በስልጣን ላይ የነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት ደግሞ በበኩላቸው ሥልጣናቸውን ላለማስነካትና በተጨማሪ ደግሞ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት የማስጠበቅ ኃላፊነት ስለነበረባቸው ተዋጊዎችን እየተከታተሉ ማጥቃታቸው አልቀረም። ስለሆነም ጦርነት ሲባል በጦር መሳሪያ መዋጋት ብቻ ሳይሆን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ፣ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የስለላ ተግባር ማካሄድ፣ አመጽ ማነሳሳት፣ ዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ አውታሮችን ማውደም ወዘተ። እነዚህ ሁሉ የጦርነት አይነተኛ ገጽታዎች ናቸው። ስለዚህ የጦርነትን ወላፈን የቀመሰ ሕዝብ ያለው አመለካከት ብዙውን ጊዜ የተዛባና የተወላገደ ቢሆን አያስገርምም።

ተበደልን ብለው ይዋጉ የነበሩት ታጋዮች ስለበዳያቸው በአንድ በኩል በእውነት ላይ የተመረኮዘ አቋም ሲይዙ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከእውነት የራቀ ነገር ቢያወሩና ቢያስወሩ አያስገርምም። ይህ ዓይነት አሠራር የትግሉ ዓይነተኛ ገጽታ ሆኖ መታየት ይኖርበታል። ይህም ከሁኔታው ጋር አብሮ  የሚሄድ ጠባይ ነው።

የተዋጊውን ኃይል ለማጠናከር ሲባል በጠላት ላይ ብዙ ኃጢአት መለጠፍ የአሰራር ዘዴ ነው።በመንግሥትም በኩል ብንሄድ የሚዋጉት ኃይሎች ተከታይ እንዳይኖራቸው፣ ዕርዳታ እንዳያገኙ፣ እንዲከፋፈሉና ውጤታማ እንዳይሆኑ ሲባል ለተነሳሱበት የጭቆናና የበደል ጥያቄ መፍትሄ በማቅረብ ፈንታ እንዲህ ናቸው፣ እንዲያ ናቸው ማለቱ አልቀረም። የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ የዚህ አይነት አመለካከት ሰለባ ነው።

ስለዚህ እንዲህ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለማረምና ለማቃናት ብሎም ትክክለኛውን መንገድ ለመከተል ይቻል ዘንድ፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በጣም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤ የስብሰባውም ዋና ዓላማ ይህ ነበር።

በአሁኑ ሰዓት የሁለቱ አገሮች ሕዝብ እንዳይገናኝና እንዳይወያይ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ የተገኘው አዲስ አበባ ያለው ሥልጣን ይገባኛል ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ የቅኝ ግዛት አድርጎ ነፃነቱንና መብቱን ነፍጎ፣ ሃብቱን ቀምቶ፣ በመርገጥና በመበዝበዝ ላይ ያለው እራሱን “የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር” ብሎ የሚጠራው ድርጅት ነው። ለኢትዮጵያ የሚያስቡትን ሁሉ “ትምክህተኞች” ይላል። ባንዳ ፉ ዘረኞች፣ ጠባቦችና ከሃዲ ባንዳዎችንስ ምን ይባሉ? ከፋፍለህ በዝብዝ የሚለውን የኰሎኒያሊስቶች እኩይ ፍልስፍና በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት ስለነቁበትና እንዳይተገበር በማድረጋቸው የፍልስፍናው አፍላቂዎች በቁጭት ላይ ይኖሩ ነበር። አሁን ግን ከብዙ ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያዊ ሀገራዊ ስሜት የሌላቸውን፣ ራስ ወዳድ የሆኑትን፣ ለግል ጥቅም አገር የሚሸጡና ከነሳቸው ውጭ ለማየት የማይችሉትን ሰዎች ለሥልጣን

እንዲበቁ አድርገዋቸዋል። ይህም ቀደም ሲል ኰሎኒያሊስቶች ሊፈጽሙ ያልቻሉትን ነገር አሁን በእጅ አዙር በወያኔ በኩል ማከናወን አስችሏቸዋል።

## "የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር"

እራሱን "ተጋድሎ ሐርነት ሕዝቢ ትግራይ" ወይም የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር ነኝ ብሎ የሚጠራው ድርጅት ብዙ የተደበቀ የባንዳነት ተልዕኮ ያለው፣ ታማኝነቱና ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ለሥልጣን ላበቁት፣ የሰላይ ድርጅቱን ላሰለጠኑለት በውጭና ለውጭ ኃይሎች የቆመ አስተዳደር ነው።

የሀገራችን መጥፊያ የሆነውን መርዝ ቀምመውና ግተው ያሰማሩት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች እንደሆኑ አንድ ቀን መረጃው በገሃድ ይወጣል። እነኚህ የውጪ ጠላቶች አማራው በኢትዮጵያዊነቱ አልበለጥላቸው ስላለ ቅስሙን ለመስበርና ብሎም በቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲጠላ ለማድረግ ያልሞከሩት ነገር የለም። ግን ይህ ሁሉ ሤራ አማራውን አነቃው እንጂ ሞራሉን አልነካውም።

የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲላላና ብሎም ጠፍቶ በጎሳ ብሔርተኝነት እንዲተካ፣ የሕዝቡ ሞራል እንዲወድቅ፣ የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማው ማድረግ፣ ወጣቱ ትውልድ ምግባረ ብልሹ እንዲሆንና በሱስ እንዲለከፍ ማድረጋቸው ሁሉ ከውጭ የተሰጣቸው መመሪያ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። እነኚህ የዓለም ሕዝብ ጠላቶች የሆኑ መሠሪ ኃይሎች ኢትዮጵያን ለማጥፋት በቀሰሙት ብልሃት ተነሳስተው ቀጥለው ሱዳንን፣ ናይጀሪያን፣ ዛየርንና ደቡብ አፍሪካን ለማጥፋት ዕቅድ አላቸው። ወያኔ የእነዚህ ኃይሎች መሣሪያ ነው።

ወያኔዎች መሪ ሆነናል ብለው 19 ዓመት ሙሉ በሥልጣን ኮረቻ ላይ ቢቀመጡም አሁንም ቢሆን ራሳቸውን "የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት" ብለው ነው የሚጠሩት። የትግራይን ሕዝብ ከማን ነፃ ለማውጣት እንዳሰቡ ቢነግሩን ጥሩ ነበር። መገንዘብ ያለብን የገሃድ ምስጢር ቢኖር - አሁንም ቢሆን መጠሪያ ስማቸውን ለመለወጥ የማይፈልጉበት ምክንያት አለ። ይኸውም መሪዎቹ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል ያላቸው የቆየ ዕቅድ እንዳለ መሆኑን የሚጠቁም ነው። ይኸም የኢትዮጵያ ጠላቶች ያወጡላቸው እቅድ ነው። ጀግናው የትግራይ ሕዝብ ግን የኢትዮጵያን ጠላቶች ሤራ ይቋቋመዋል እንጂ ቅጥረኞቹን በፍጹም አይከተልም ብለን እናምናለን።

በርከት ያሉ የአግዓዚ ክፍለ ጦር ወታደሮች ኢትዮጵያዊ ወገናችንን አንጨፈጭፍም ብለዋል። ብዙዎችም በ97 ምርጫ ቅንጅትን መርጠዋል። ወያኔ ምን ይበል? እነ መለስ ዜናዊ፣ ስብሃት ነጋ፣ ሰሎሞን እንቋይ የመሳሰሉትና የእነርሱ ቀኝ እጅ የሆኑት ሁሉ እራሳቸውን በትግራይ ሕዝብ ስም ስለጠሩ የትግራይን ሕዝብ ይወክላሉ ወይ? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው። መልሱ አይወክሉም ነው። የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የማይሰረዝና የማይደለዝ ቦታ ያለው ሕዝብ ስለሆነ በስሙ መነገድ ያለቀለት የቸርቻሪ ነጋዴ ብልጣብልጥነት ነው። ኢትዮጵያ በውጭ ጠላት በተወረረችበት ዘመን ሁሉ በመጀመሪያ ደረቱን ለጥይት የሚሰጠው ይኸ ሕዝብ ነበር። ከግራኝ መሐመድና የሱዳን መሃዲስቶች ጋር በተደረገው ጦርነት ተገቢ ቦታውን ይዞ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር ጠላትን የተናነቀ ይኸው ሕዝብ ነበር። ቱርኮች፣ ግብጾችና ጣልያኖች ኢትዮጵያን ሲወሯት የጦር አውድማ የሆነው የትግራይ መሬት ነበር።

እንደ አፄ ዮሐንስ፣ ራስ አሉላ፣ ዘርዓይ ድረስ፣ ዓውአለም ወልዱ የመሳሰሉ ጀግና ኢትዮጵያውያን በተወለዱባት አገር፣ የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነውና እንደ መለስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ የመሳሰሉ የአስተዳደግ ጉድለት ያለባቸው ከሃዲዎች የስብዕና ጉድለት የተጠናወታቸው፣ ለሰው ልጅ ፍቅር ሳይሆን ጥላቻ፣ አክብሮት ሳይሆን ንቀት ያላቸው ጉደኞች ቢበቅሉባት ሊያስደንቀን አይገባም። በእብሪት የተሞላ ሰው ሁሉን አዋቂ ሁሉን ናቂ ስለሆነ "አማራው ታሪክ በመተረክ የሚኖር የወረቀት ነብር ነው" ይላሉ። እውነቱን ግን ታሪክ ይመስክር ብለን እናልፈዋለን።




*ስዕል 1: ከጐንደርና ወሎ ክፍላተሃገራት ተቆርሰው ወደ ትግራይ ክ/ሃገር በወያኔ የተቀላቀሉ ወረዳዎች*

ወያኔዎችን መርምረው ሳያውቁ በየዋህነት፣ ወይንም በጥቅም ተገፋፍተው የሚደግፉ የትግራይ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፣ በአንፃሩ ደግሞ በኢትዮጵያዊነታቸው ፀንተው ሽንጣቸውን ገትረው ድርጅቱን በመቃወም የሚታገሉ ብዙዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ከመካከላችን የሚገኘው ወንድማችን ዶክተር አረጋዊ በርሄ ነው። በቅርቡ ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ከሰጠው ቃለ መጠይቅ ልጥቀስ፡- "<u>የጐንደርንና የወሎን ሕዝብ ሳናስፈቅድ መሬቱን ቀምተን ወስደን ትግራይ ውስጥ መቀላቀላችን ትልቅ ስህተት ነው</u>" ብሎ የተናገረውን ቃል ብዙ ኢትዮጵያውያን ስላደመጡ ከበሬታን አትርፎለታል። የፖለቲካ ሰዎች ቢያምታቱ አያስገርምም። ከአንድ ምሑር ግን የሚጠበቀው እንደዚህ ያለ በዕውነት ላይ የተመረኮዘ ትክክለኛ የሆነ አቋም ነው። የሕዝብ አመኔታ በቀላሉ አይገኝም። ብዙ ፈተናን ማለፍ ይጠይቃል። "የሕዝብ መብት"፣ "ሥነ-ምግባር"፣ "ህገ-መንግሥት"፣ "ዲሞክራሲ"፣ "እራስን በራስ የማስተዳደር መብት" እያሉ እነ መለስ ዜናዊ የሚመጻደቁበት አምታችነት ሁሉ እርባና እንደሌለው ከወሎና ከጐንደር በቅኝ ግዛትነት ከተያዙት ወረዳዎች መገንዘብ ይቻላል።

በአንፃሩ ግን የሐርነት ትግራይ "የጀግናዋ ትግራይ" መሪ አቶ ገብሩ አሥራት በበኩሉ የትግራይ "ክልል" አስተዳዳሪ በነበረበት ጊዜ የወልቃይትን ሕዝብ "ባርኖስ" ወይም "ትል" ብሎ የዘለፈ ሰው፤ ይህ አልበቃው ብሎ በቅርቡ በዋሺንግተን ዲ.ሲ. በተደረገ ስብሰባ ላይ ደግሞ በወያኔ የቅኝ ግዛትነት ሥር ስለወደቀው የወልቃይት ፀገዴ ሕዝብ ሥቃይ ቢጠየቅ የሚናገረው ቢያጣ "<u>እኛም የጨው መሬታችንን</u>" አስረክበናል ብሎ አሾፈ። ለማን እንዳስረከበ፣ በምን ምክንያት እንዳስረከበና እንዴት እንዳስረከበ አላብራራም። መሬቱን ተቀምቶ በስደትና በችግር የሚሰቃየውን የሕዝብ ጥያቄ ከጨው መሬት ጋር ማወዳደሩ ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ ነኝ ከሚል ሰው የሚጠበቅ አልነበረም። "ትግራይ የተማረ ሰው የላትም፣ የማዕድን ሃብት የላትም፣ የእርሻ መሬት የላትም" ይላል መለስ ዜናዊ። ስለዚህ የሁመራ፣ የወልቃይት፣ ፀገዴ፣ የዳንሻና የራያ እርሻ መሬቶች በትግራይ ቁጥጥር መሆን አለባቸው ማለት ነው? የትግራይም ድንበር ማይጨው ሳይሆን አሸንጌ እንዲሆን ተደረገ።

ምክንያቱ ይኸው ነው። በድንቁርና ላይ ጥላቻ፣ በቂመኛነት ላይ ሥልጣን፣ በአብሪት ላይ ስካር ሲጨመርበት ውጤቱ በጣም አሳዛኝ ይሆናል።

## ማካካሽ ሊሆን አይችልም

የወያኔን መሪዎች ዓላማ የሚቃወመው በጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሆነ ሕዝቡን እየከፋፈሉና እያጋጩ ማዳከም አለባቸው። የሴራቸው የመጀመሪያ ሰለባ የሆነው አማራው ነው። ልማት የሚባል ነገር የአማራው ሕዝብ ከተነፈገ እንሆ ሃያ ዓመት ሊሆን ነው።

የተከዜን ወንዝ ተሻግረው የጐንደርን ሕዝብ መሬት በወረራ ከያዙ በኋላ አብዛኛውን ኗሪ ሕዝብ ከመሬቱ ነቅለው አባረውታል። በወረራ የተያዘው የወሎም መሬት ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። ነፃ ለምትወጣው "የትግራይ ሪፑብሊክ" ለማግኘት የሚፈልጉትን የፖለቲካና የዲፕሎማቲክ ድጋፍ ተጨባጭ የሆነ ዋስትና እንዲኖራቸው ለማድረግ ታሪካዊ የሆነውን የኢትዮጵያ መሬት (ፊርማቸው ዋጋ ካለው) ፈርመው አስረክበዋል። መዋሸትና ማምታታት የግል ባህላቸው ያደረጉ ሰዎች አሁንም አልሰጠንም እያሉ ሕዝቡን ለማተለል ይሞክራሉ። ሁኔታውን በጠቅላላ የምናውቅ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስላለን መሬቱ የኢትዮጵያ ለመሆኑ የሚያረጋግጡ ብዙ መረጃዎችን ለማቅረብ እንችላለን፤ ለወደፊቱም እናቀርባለን። አምስት ሚሊዮን የሚያህል ሕዝብ እየተራብ ባለበት ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ኢትዮጵያውያን በዚሁ ለም መሬት ላይ አሥፍሮ ምርታማ ገበሬዎች ማድረግ ሲቻል ለሱዳን ፈርመው ማስረከባቸው በሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነት ምንም እንደማያስቡ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ሊያውቀው የሚገባ ከፍተኛ የሆነ የወንጀል ሥራ አለ። ይኸውም ወራሪዎቹ የወልቃይትና ፀገዴን ልጃገረዶችና ሴቶች በግድ በመድፈርና በማስረገዝ የኗሪውን ሕዝብ ዘር እና አይነት ለመለወጥ አማረነቱና ጎንደሬነቱ እንዲጠፋ ለማድረግ ዓላማ አላቸው። ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በዚህ ዓመት ብቻ የተወለዱ አባት የሌላቸው 82 ህፃናት አሉ። ይህንንም ወንጀል የተባበሩት መንግሥታት ኃላፊዎች እንዲመረምሩት እንጠይቃለን። እንደዚህ ያለ ወንጀል በዝምታ ሊታለፍ አይችልም።

የሂትለር ተከታዮች በእሥራኤሎች ላይ ከፈጸሙት ግፍ መለስ ዜናዊ፣ ስብሃት ነጋ፣ በረከት ስምኦን፣ ሙሉጌታ ዓለምሰገድ፣ ስዩም መስፍን፣ አባዲ ዘሙ፣ ገብሩ አሥራት፣ ፀጋዬ በርሄ፣ ሰለሞን ዕንቋይ፣ ወዘተ የመሳሰሉት የህሊና ወቃሽ የሌላቸው ሰዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በጠቅላላ የፈፀሙትና የሚፈጽሙት ወንጀል ይበልጣል።

መሬቱን የተነጠቀው ሕዝብ የት ይግባ ተብሎ መለስ ዜናዊ ቢጠየቅ የሚከተለውን መልስ ሰጠ፦ "በመሬቶቹ ላይ ሰፍረው የሚገኙት የትግራይ ገበሬዎች በኑሯቸው ስለተደላደሉ ማነቃነቅ አይቻልም። [ለተፈናቀለው] ሕዝብ ሌላ መሬት ተፈልጎ እስኪሰጥ ድረስ መጠባበቅ ይኖርባቸዋል።" የወልቃይትና የፀገዴ ሕዝብ ከአያቱና ከቅድመ አያቱ በወረሰው መሬት ላይ የትግራይን ወታደርና ገበሬ ከማስፈር፣ ለምን ለእነሱ አዲስ መሬት ተፈልጎ አይሰጣቸውም? ደቡብ አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት ይረግጡ የነበሩት ዘረኛ ነጮች የሚናገሩት መለስ ዜናዊ ነጭ ነኝ ካላለ በስተቀር ቋንቋውና አስተሳሰቡ ተመሳሳይ ነው።

አስረክበን ለሚሉት "የጨው መሬት" የጐንደር ሕዝብ መሬት ማካካሻ ሊሆን አይችልም። ወያኔና የትግራይ ብሔርተኞች ማወቅ የሚገባቸው ነገር ቢኖር ወደዱም ጠሉም በቅኝ ግዛትነት የተያዘው ሕዝብና መሬት ነፃ ይወጣል። ይህም የጊዜ ጉዳይ ነው። በወያኔ የተዘረፈው፣ መሬቱን የተቀማው፣ ቤቱን ያቃጠሉበት፣ ሚስቱና ሴት ልጆች የተደፈሩበት፣ በግፍ ላይ ግፍ የተፈፀመበት ሕዝብ ምን እንደሚያደርግ ለማወቅ ፈላስፋ መሆን አያስፈልግም።

የወልቃይትን ፀገዴ ሕዝብ መጋቢት 3 ቀን 2002 ዓም በወሰደው እርምጃ ሁመራና በአካባቢው የተቃጠለው 816 ቤት፣ 1456 ኩንታል ሰሊጥ፣ 1118 ኩንታል ማሽላ፣ 9 ኩንታል ጤፍ፣ ከ3000 በላይ የሚሆን ሕዝብ መፈናቀል ትርጉሙ ምን ይሆን? በሆነው ባልሆነው በኤርትራውያኖች ማመካኘት ዕርባና የለውም። የተበደለ ሕዝብ እንኳን ይሄን ሌላ ይሰራል።

ጐንደርንና ሁመራን በሚያገናኘው መንገድ ላይ ዳንሻ ትገኛለች። ወያኔ በትግራይ ዋሻዎች ያጠራቀመው የጦር መሣሪያ አለበቃ ብሎት አሁን ደግሞ የጐንደርንና የኤርትራን ሕዝብ ለመደብደብ ይረዳው ዘንድ ዳንሻ ላይ ቦንብ የሚጭኑ አውሮፕላኖች የመሬት ውስጥ ማቆሚያ ሰርቷል።

የወያኔ የማጥቃት ዘመቻ በጐንደርና በወሎ ሕዝብ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ነው እንዳይባል ከደቡብ፣ ከምሥራቅና ምዕራብ ኢትዮጵያ ተወልደው ካደጉባቸው ክፍላተ ሃገራት እየተነቀሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አማራዎች እየተባረሩ ነው። ለምሳሌ ያህል በሐምሌ ወር 2002 ዓም ብቻ 12,000 የሚሆኑ አማራዎች - ህፃናት፣ ነፍሰጡር ሴቶችና ሽማግሌዎች ሳይቀሩ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል እንዲባረሩ ተደርጓል። በመሀይሙና በአድርባዩ ታምራት ላይኔ አነጋገር "ከክልላችን ውጭ ያለ አማራ በሙሉ ነፍጠኛ ነው። በነፍጠኝነት ሌሎችን ሊገዛ ሄዶ ነው እዚያ የቀረው" አለ። የኢትዮጵያን ታሪክ ያላነበበ ሰው ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ምስክር የለም።

የጐንደርን መሬት ነጥቀው ከትግራይ ጋር የቀላቀሉት የክፍለ ሀገሩን የተፍጥሮ ሀብት በመሻት ብቻ ሳይሆን የሱዳንን ጉርብትና ለማግኘትና ነፃ ለምትወጣው "የትግራይ ሪፑብሊክ" በሱዳን በኩል የባህር በር እንዲኖራት ለማድረግ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ መቀሌንና ጎዳሪፍን የሚያገናኝ አውራ መንገድ በመሥራት ላይ ነው። የባቡር ሃዲድም ለመዘርጋት ፍላጎት አላቸው። በ$400 ሚሊዮን ዶላር የተከዜን ግድብ ማሠራት፣ በ$300 ሚሊዮን ዶላር ትግራይ ውስጥ Wind Mill ማቋቋም፣ የዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያዎች፣ ፍብሪካዎች፣ ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮሌጆች፣ የከተማ ቤቶች፣ ወዘተ የተሠሩት ዋነኛ ምክንያት ነፃ ለምትወጣው ትግራይ ምሰሶ እንዲሆኑ ነው።

ሌሎችም እንደ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ወያኔን የሚታገሉ የትጋራይ ልጆች አሉ። ከእነዚህ መካከል ትልቁ  ገብረ መድህን ዓርአያን፣ የእነ መለስ ዜናዊንና ስብሃት ነጋን ከሃዲነት፣ ፀረ ኢትዮጵያዊነት፣ ዘራፊነትና አገር ሻጭነት ቀደም ብለው የተገነዘቡት እነ ካህሳይ በርሔ፣ ተስፋየ አጽብሃና ሌሎችም ይገኛሉ።

"ትግራይ ራሷን ችላ ለመጓዝ እንደምትችል መገመት ይቻላል" ይላል መለስ ዜናዊ [ትርጉም] "ካስቸገራችሁኝ ትግራይን ለማስገንጠል ያወጣሁትን ዕቅድ በሥራ አውላለሁ። ይህ ካልተሳካልኝ ግን በቂ ገንዘብ ስለዘረፍኩ ቤተሰቤን ይዤ የትም አገር ሄጀ መኖር እችላለሁ" ማለቱ ነው። ይቻላል ወይ?

ስብሃት ነጋ በበኩሉ እንዲህ ይላል፡- "የትግራይ ጥያቄ ልክ እንደ ኤርትራ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው።" ማለት ብቻ ሳይሆን "እኛ ሥልጣን ከለቀቅን ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም" አለ። ኢትዮጵያ ከወያኔ በፊት አልነበረችም ማለት ነው? ወይስ አጥፍተናት እንሄዳለን ማለት ነው? መለስ ዜናዊ በበኩሉ በፉከከሩ እንዳይበለጥ እንዲህ ይላል፡- "የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳያችን አይደለም፣ አብረንም አልኖርንም፣ አታውቁንም፣ አናውቃችሁም፣ ወርቅና አፈር አንድ ላይ አይቀላቀልም" [ትርጉም]፤ የእኛን ጭቆናና ዝርፊያ ጭጭ ብላችሁ ካላተቀበላችሁ ወስዳችሁ ዛፍ ላይ ከምትሰቅሉን አገሪቱን አጥፍተን የትግራይን ነፃነት አውጀን የምንኖርበትን ዕቅድ አዘጋጅተናል።

ነገሩ ሁሉ እንዲህ ከሆነ ለምንድን ነው ወያኔዎች በሥልጣን ላይ አሁንም ያሉት? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው። መልሱም ግልፅ ነው፤ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች አገራችንን ለማጥፋት በቀጥታ መንገድ ስላልቻሉ አሁን በሌላ መንገድ መጡብን፤ ወያኔዎችን አሰልጥነውና በየጊዜው ምክሮችን እየለገሱ በሥልጣን ኮረቻ ላይ ያስቀመጧቸው ይመኙት የነበረውን ኢትዮጵያን ያማጥፋት ዓላማ በእጅ አዙር እንዲያከናውኑላቸው ነው። በዛውም ላይ ዝርፊያውን በማስፋፋት "ነፃ" ለምትወጣው ትግራይ የሚሆን ገንዘብ ለማጠራቀም ነው።

ይህንን መንግሥት የምንቃወመው ሁሉ ተቃውሟችን በትግራይ ሕዝብ ላይ የተነሳሳ አለመሆኑን መታወቅ ይኖርበታል፤ ትግላችን በትግራይ ሕዝብ ስም የሚነግደውን፣ የሚዘርፈውን፣ ሕዝባችንን የሚጨፈጭፈውንና አገራችንን በማጥፋት ላይ ባለው ቅጥረኛ መንግሥት ላይ ያነፃፀረ ነው።

የትግራይ ሕዝብ እንደሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመረገጥ ላይ ነው። ለትግራይ ሕዝብ በዕርዳታ ስም የመጣውን እህል መሪ ነን ባዮች ሸጠው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ወንጀለኞች ናቸው፤ ከ13,000 በላይ የሚሆነውን የትግራይ ሕዝብ በርሃብ እንዲያልቅ ያደረጉ፣ ከ20,000 በላይ የሚሆነውን የትግራይ ወጣት በማያውቀው ፖለቲካ አስገብተው በጦር ሜዳ እንዲያልቅ ያደረጉ፣ ከ40,000 በላይ የሚሆነውን የትግራይ ተወላጅ በአሰቃቂ የጉድጓድ እስር ቤት አጉረው የሚያሰቃዩ ሰዎች ናቸው። ታዲያ እነዚህ ናቸው ነፃ አውጪዎቹ?




*ስዕል 2: ወያኔ ትግራይን ለማስገንጠል ከጐንደርና ወሎ ለም ወረዳዎችን በመጨመር እኤአ በፌብሯሪ 1976 በማኒፌስቶው ያወጣው የ"ታላቋ ትግራይ ሪፑብሊክ" ካርታ*

ስለዚህ ለትግራይ ሕዝብ የቆሙ ናቸው ብሎ መናገሩ ትልቅ ስህተት ነው። ከትግሬዎች ሌላ የወያኔ መሣሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ኦሮሞዎች፣ ጉራጌዎች፣ አደሬዎች፣ አማራዎች የሉም ለማለት ነው? ሐረርን እንዲያስተዳድርላቸው የሾሙት አንድ አድርባይ አደሬ የሚናገረው ቢያጣ "አፄ ምኒሊክ የ250 ዕርጉዝ ሴቶችን ጡት ሐረር ከተማ ላይ ቆርጧል" ብሎ ሲለፈልፍ ሕዝቡ ሁሉ ሰምቶታል። እንደዚህ ያለ አሳፋሪ ውሸት የሚናገር ሰው በኃላፊነት ቦታ እንዲቀመጥ ያደረጉት የወያኔ ባለሥልጣኖች ከተናጋሪው ሰውዬ ብዙም እንደማይለዩ ብዙዎቻችን ከተገነዘብን ቆይተናል። እንደዚህ ያለው ቀጣፊና ውሸታም ሰው በቦታው መቀመጡ ብቻ የወያኔን ባለሥልጣኖች ምንነት በደንብ ያንፀባርቃል።

ወያኔዎች በእውነትና በውሸት መካከል ያለውን ልዩነት እንኳ ለመገንዘብ የሚያስችል ህሊና ያላቸው አይመስለኝም። ምክንያቱም ውሸትን፣ ቅጥፈትን፣ ስርቆትን፣ ዝርፊያንና ግድያን ሁሉ ሥራዬ ብሎ አንድ ሰው እንደ ሞያ ከያዘው ተግባሩ ከሰውነቱ ጋር ይዋሃድና ሌላ ነገር ማሰብም መሥራትም ይሳነዋል። ሕዝብ በሚራብበትና በሥራ አጥነት በሚሰቃይበት አገር ኢኮኖሚው በ10% በየአመቱ ያድጋል ብለው ሲናገሩ የዚሁ አመላቸው ነፀብራቅ ነው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር በቅርቡ ያወጣው ጥናት እንደሚጠቁመው ኢትዮጵያ በዓለም ውስጥ ካሉት አገሮች የመጨረሻዋ ደሀ ነች። በፍፁም ደሀ ተብለው ከተመደቡት አስር አገሮች ውስጥ መንግሥት የሚባል ነገር የሌለባት አገር ሶማሊያ እንኳን ከኢትዮጵያ የተሻለ ደረጃ ይዛ ትገኛለች። ማለቂያ የሌለው የወያኔ ቅጥፈትና ውሸት ተጋለጠ። "ኢኮኖሚው ከ10% በላይ በየአመቱ እያደገ ሄዷል"፣ "በ5 ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያ የምግብ እህል ወደ ውጭ አገር ገበያዎች ታቀርባለች" ወዘተ ይላሉ። በ5 ዓመት ውስጥ ጨረቃ ላይ እናርፋለን አለማለታቸውም ትልቅ ነገር ነው።

ሁሉ ነገር አላዋጣ ስላለ አሁን ደግሞ ለእነሱ አወናባጅነት አልንበረከክም ያሉትን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስም የማጥፋት ዘመቻ ቢጀምሩ አያስገርምም። ሁሉንም ሌባ፣ ቀጣፊ፣ ዘራፊ፣ ዝሙተኛ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ማጅራት መቺ፣ ሰላይ፣ ወዘተ እያሉ ልዩ ልዩ ቅጽል ስም እያወጡ ቢለጥፉ መገረም የለብንም። ሞራልና ግብረገብ ከሚጎድላቸው ህሊና ቢስ ሰዎች ምን ይጠበቃል?

በቅርቡ ተካሄደ የሚሉትን ምርጫ ሙሉ በሙሉ አሸነፍን ስላሉ መደነቅ የለብንም። ምክንያቱንም ተናግረዋል። ሕዝቡ ይህን ያህል የሚወዳቸው ከሆነ ለምንድን ነው መለስ ዜናዊ ከአራት ኪሎ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ እንኳን ሲሄድ ትራፊክ በሙሉ ተዘግቶ በ35 የልዩ ጥበቃ መኪናዎች ታጅቦ የሚሄደው? እስከዚህ ሰው የሚወደው "መሪ" ከሆነ ለምንድን ነው ወጣ ብሎ ጐንደር፣ ሐረር፣ጂማ፣ ነቀምት፣ መቀሌ፣ ደሴ ሊጐበኝ ሄዶ ፊቱን የማያሳየው?

በኑሮ ውድነት ምክናያት የሚማቅቀው የከተማ ሕዝብ፣ በቋፍ ላይ ያለው ወታደር፣ በመንገፍገፍ ላይ ያለው የወያኔ ጭሰኛ የሆነው ገበሬ፣ ደመወዝ እየተባለ የኪስ ገንዘብ የሚከፈለው ወዝ አደር፣ ቋቅ ያለው ተማሪና አስተማሪ፣በረሃብ አለንጋ የሚገረፈው 5 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ፣ 256,400 ዕሥረኛ፣ ከመሬቱ የተፈናቀለው 839,000 አማራ፣ በሥራ አጥነት የሚንገላታው ከተሜ፣ በሺህ የሚቆጠረው ለማኝ ሁሉ የእነርሱን አስተዳደር ተስማምቶናል ኑሯችንም የተደላደለ ሆኗል ብሎ መረጣቸው ማለት ነው? ምን ይታወቃል ብዙ ነገር ገና እንሰማለን። የናፈቀኝ ነገር ቢኖር በትክክለኛ መንገድ ተጠንቶ የተፃፈ የእነርሱን ታሪክ ለዓለም ሕዝብ የሚያቀርብ መጽሐፍ ነው።

## "አናውቃችሁም"

መለስ ዜናዊ "አናውቃችሁም" ስላለ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ዓይነት ሕዝብ እንደሆነ ለማወቅ ይረዳው ዘንድ የሚከተለውን ዘገባ በጥሞና ይመለከተው ዘንድ አቅርበናል።

ሌ/ኮሎኔል ጌታቸው መንገሻ የሚባል ኢትዮጵያዊ የአገሩን ዳር ድንበር ከጠላት የተከላከለ፣ ኢትዮጵያ በምትፈልገው ጊዜ ያለማወላወል የዜግነት ግዳጅን ደጋግሞ ያበረከተ ጀግና የኢትዮጵያ የአየር ኃይል አባል፣ ከምድር በተተኮሰ የወያኔ ሚሳይል የሚያበራት mg-21 አውሮፕላን ተመታ ከወደቀች በኋላ የጐንደር ሕዝብ እርሱን ከወያኔ ወታደር ተከላክሎ ደብቆ እንዴት እንዳዳነው ኰሎኔሉ ከተናገረው እንጥቀስ፦

> "ደቡብ ጐንደር ለአንድ ወር ያህል በገጠር ስቀይ ያስጠጉኝ ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው ህይዎትና ደህንነት ይልቅ ለእኔ ህይዎትና ደህንነት ቅድሚያ ሰጥተው ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ትኩስ ውሃ ይዘው አምጥተው እግሬን አጥበው ከጨረሱ በኋላ (እግሬን ስመው ነበር የሚያስተኙኝ። የሚለብሱትን ልብስ አውልቀው እኔን አልብሰውኛል። የሚተኙበትን ቦታ ለእኔ ለቀው መሬት ተኝተዋል። እነርሱ ጦማቸውን እየዋሉና እያደሩ እኔን አብልተውኛል። የእርሻ ሥራቸውን ትተው እኔን ከቦታ ቦታ በማነቃነቅ ለቤቴ ለደብረዘይት እንድበቃ አድርገውኛል።"

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላ እንደዚህ ያለ ሕዛብ ነው። የአንድን አገር ሕዝብ ባህልና ታሪክ ሳያውቁ "መሪ" ነኝ ማለቱ ችግሩ እዚህ ላይ ነው። "የአክሱም ሃውልት ለወላይታ ምኑ ነው?" "የጐንደር ግንብ ለጋምቤላ ምኑ ነው?" ብሎ መጠየቁ ብልጣብልጥነት ቢያስመስልም የእውቀት ምልክት ሳይሆን የመሃይምና የደንቆሮ ጥያቄ ነው። አንድ ሰው መሪ ከመሆኑ በፊት ተመሪ መሆን አለበት።

አፄ ቴዎድሮስን በቅርብ የሚያውቅ ቫልድማየር የሚባል እንግሊዝ ስለ እርሳቸው ከተገነዘበው በትንሹም ቢሆን እንጥቀስ፦ "የወታደሮቹን ኑሮ የሚጋራ፣ የዘመናዊ ሥልጣኔ ሀሳብ የገባው ንጉሥ፣ ኃይልና ታላቅነት ሳያንሰው የምቾትና የቅምጥል ኑሮ የማያታልለው እንዲህ ያለ ንጉሥ የት ይገኛል?"

የታሪክ ምፀት ሆነና፣ እነ አፄ ቴዎድሮስ እና አፄ ምኒሊክ በተቀመጡበት ወንበር ላይ መለስ ዜናዊ መቀመጡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ስድብ ነው። ከየት እንደመጣ እንኳ እረስቶ በየስድስት ወሩ ከእንግሊዝ አገር ልብስ ሰፊ እያስመጣ ወገቡንና አንገቱን ያስለካል። በባዶ እግሩ እንዳላደገ ሁሉ 7,500 ብር የሚያወጣ ሱፍ ልብስ ይለብሳል። የሕዝቡን ኑሮ መኖር ማለት ይኸ ነው? አልቤንያን ሶሻሊዝም፣ የትግራይ ማርክሲስት ሊግ ዋና ፀሐፊ ማለት ይኸው ነው? ወይንስ ለማወናበጃ ሽፋን

መሆኑ ነው? አራስ ነብሪቱ እቴጌ ጣይቱ በተቀመጡበት ወንበር ከሃዲቱ አዜብ መስፍን ተቀምጣ የተወለደችበትን አገር ሳይቀር በመሸጥ ላይ ትገኛለች።

## <u>አንድ መቶ ሃምሳ (150) ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ የት ይግባ?</u>

በቅርቡ የዓለም ባንክ ያደረገውን ጥናት ብንመለከት፣ ከአርባ ዓመት በኋላ ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 150 ሚሊዮን ይሆናል ተብሎ ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ከ 50 እስከ 60 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ በልዩ ልዩ ተግባር ተሠማርቶ በከተሞች ውስጥ ቢኖር፣ 100 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ ደግሞ በእርሻ ሥራ ላይ መዋል አለበት። ደጋው የኢትዮጵያ መሬት ለ4,000 ዓመታት ያለማቋረጥ ስለታረሰ መሬቱ ተበልቷል፣ ደክሟል፣ ይኸን ያህል ሕዝብ ለመደገፍ ያለው አቅም መንምኗል።

በወያኔ ኢትዮጵያ 40% የሚሆነው ገበሬ በነብስ ወከፍ የያዘው የእርሻ መሬት ስፋት 0.5 ሄክታር ሲሆን፤ ትንሽ ይሻላሉ በተባሉ መሬቶች ላይ ያለው ገበሬ 60% የሚሆነው እያንዳንዱ የያዘው መሬት ከአንድ ሄክታር እንኳ የማይበልጥ መሬት ይዞ ትምህርትና ቴክኖሎጂ ባላደገበት አገር፣ አስተማማኝ ዝናብና ሌሎች ምርትን ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ መገንቢያዎች በሌሉበት ሁኔታ ገበሬው እንኳንስ ኢትዮጵያን በምግብ እራሷን እንድትችል  ማድረግ ቀርቶ ቤተሰቡን እንኳን መመገብ አይችልም። ይኸውም ችግር መለስ ዜናዊና  ደጋፊዎቹ በሕዝብ ላይ ከከፈቱት ጦርነት አንዱ ገፅታ ነው።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምና ዕድገት የሚያስብ መንግሥት ቢኖር ኖሮ ፣ አገሪቱ ምንም ጥቅም ለማታገኝበት አሠራር የውጭ ነጋዴዎችን ጋብዞ እርሻቸውን አቋቁመው እንዲያርሱ ሰብሉንም እንደፈለጉት እንዲያደርጉ ስምምነት አያደርግም ነበር። ከሚከፍሉትም ኪራይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድም ጥቅም አያገኝም። አፈሩን በማበላሸት፣ ደኑን በማጥፋትና ውሃውን በመመረዝ አገሪቱን ምድረበዳ ከሚያደርግ አደጋ ላይ ነው የወደቀችው። ለኢትዮጵያ ገበሬ ቅድሚያ መሰጠት ነበረበት። የሚያርሰውን ገበሬ በዚሁ መሬት ላይ ማስፈር በተቻለ ነበር። ገበሬው የያዘውን የመሬት ስፋት ከፍ ማድረግ ይቻል ነበር። በሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ግን ፍላጎታቸው ይኸ አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም።

ሰው፣ ሴቱ፣ ወጣቱ፣ መሬቱ፣ ማዕድኑ፣ ደኑ ሁሉ እየተሸጠ ነው። ለምሳሌ ያህል ያለፉት መንግሥታት ተንከባክበው ያኖሩት ጅማ ላይ ያለው ደን እየተመነጠረ ለሳውዲ አረቢያ  እየተሸጠ ነው። አንድ ሰው ከጅማ እስከ  አዲስ አበባ ያለውን መንገድ ይዞ ቢሄድ የሚያየው የአበባ እርሻ ብቻ ነው። ለምን? የትም አገር ተደርጎ  የማይታወቅ አንድ ጋሻ መሬት በ$1.00 ኪራይ ለመቶ ዓመት ለህንዶች ተሰጥቷል። እነርሱም ባቄላ፣ ምስር፣ አተር ወዘተ እያመረቱ ለህንድ ገበያ ያቀርባሉ። በዚህ ዓይነት ውል የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያገኘው ጥቅም ምን ይሆን? ተጣብቦ የሚያርሰው ኢትዮጵያዊ ገበሬ ሲሆን በነፃ ካልሆነ ደግሞ ለህንዶች የተሰጠው ዓይነት መሬት ለምን አይሰጥም?

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስብ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ ለገበሬው የተፈለገውን ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል። አገሪቱ በምግብ እራሷን እንድትችል አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ ወደኋላ ማለት የለበትም። ገበሬው በፋንታው እራሱንና ቤተሰቡን ከመደገፍ አልፎ አገር ውስጥ የሚመረቱትን የፋብሪካ እቃዎች የመግዛት አቅም ስለሚኖረው እየተስፋፋ ለሚሄደው ኢንዱስትሪ ምሰሶ መሆን ይችላል። ኢንዱስትሪን በእርሻ፣ እርሻን በኢንዱስትሪ መገንባት ይቻላል። ይህን ለማድረግ ግን ለአገር ማሰብን ይጠይቃል። ይህም ማለት ኢትዮጵያ መመራት ያለባት ከግል ጥቅም ይልቅ የሕዝቡን ጥቅም በሚያስቀድሙ ሰዎች ሲሆን ነው። አሌክሳንደር ሃሚልተን (አሜሪካ)፣ ሜጅ (ጃፓን)፣ ሳንያትስን (ቻይና)፣ አታቱርክ (ቱርክ)፣ ጋንዲ (ህንድ)፣ ጋማል አብደልናስር (ግብፅ)፣ ሪዛ ሻህ (ፐርዥያ)፣ የመሳሰሉት መሪዎች የተከበረ ቦታ በታሪክ ገጾች ላይ ሊይዙ የቻሉት አገራቸውን ሲመሩ በጎጠኝነትና በጎሳ ፖለቲካ በመነከር ሳይሆን ሁሉንም በአንድ ዳስ ውስጥ በመሰብሰብ በብሔራዊነት፣ እኩልነትና ነፃነት ፍልስፍና በመምራት ነበር።

ዘረኝነትን ለመዋጋት ዘረኛና ጎጠኛ መሆን ሳይሆን ሁሉንም በሚያሰባስበው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና በኢትዮጵያ ብሔርተኝነት ሥር ተሰልፎ መታገል ብቻ ነው።

ወያኔዎች የሐገር ምሰሶ የሚሆነውን ትውልድ ግማሹን ሲጨፈጭፉ ግማሹን እንዲሰደድ አድርገውታል። ይህ ከሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ ስደተኛ ግን እየተማረ፣ እውቀት እያካበተ፣ ንብረት እያፈራ፣ ዘመዶቹን እየረዳ ቀን በመቁጠር ላይ

ይገኛል። ወያኔዎችና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ወደዱም ጠሉም የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከጠበቁት በላይ እያየለ መጥቷል።

## የልማትና የዕድገት ፖሊሲ ምርምር ማዕከል

ከ104 ዓመታት በፊት አለቃ ታየ ለአፄ ምንሊክ ከጀርመን አገር ከጻፉላቸው ደብዳቤ ውስጥ የሚከተለውን ልጥቀስ፡-

> "በአገራችን ጥቂት እውቀት ያላቸው ሰዎች በመከበር ፈንታ ስለሚሰደቡና ስለሚዋረዱ፣ የሚያውቁትን ጠቃሚ የጥበብ ሥራ ትተው በቦዘን መኖርን መረጡ። የእኛ ሰዎች መጽሐፍ ቢማሩ ኮቸሮ ለቃሚ፣ እንጨት ቢሰሩ አናጢ፣ እንጨት ቆርቋሪ፣ ቆዳ ቢፍቁ ጥንብ በላ ፋቂ እየተባሉ ለሥራው ሁሉ ስም እየተሰጠ ስለሚሰደቡ የጥበብ ሥራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀዘቀዘ ጠፋ።"

አለቃ ታየ ይህን ደብዳቤ በጻፉ በ52ኛው ዓመት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በሐምሌ 16 1950 ዓም አዲስ አበባ የሚገኘውን ታዋቂ የሆነውን የስዕል ትምህርት ቤት በከፈቱበት ቀን የሚከተለውን ተናግረው ነበር።

> "ታላቅ ሞያ ያላቸው ወጣቶች ሁሉ ጥንታዊውን አሠራር ሳይለቁ ከዘመናዊው አሠራር ጋር እያዋሃዱ የኪነ ጥበብ ሥራ በአገራችን እንዲታደስና ይበልጥ እየተስፋፋ እንዲሄድ ያማድረግን ጉዳይ ታላቅ ቁም ነገር ስለምንሰጠው ነው። ለዚህም ኢትዮጵያ የሥላጣኔን ባሕልና መንፈስ ተከታይ መሆኗን ለማሳወቅ ለሚደረገው ጥረት ድጋፍ ይሆናል ብለን ተስፋ የምናደርግበት ነው።"

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተናገሩት ቃል ጠቃሚ ነበር። ስለሆነም ንግግራቸው በስዕል ሥራ ላይ ብቻ ማተኮር ሳይሆን በጠቅላላ ትምህርትን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን፣ ልማትና ዕድገትን በአገር ደረጃ ለማስፋፋት ይቻል ዘንድ አንድ የልማት የፖሊሲ ምርምር ማዕከል በገንዘብና ብቃት ባላቸው ሞያተኞች አጠናክሮ ኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፍ መከተል ያለባትን አቅጣጫ እንዲተልሙ ቢደረግ ኖሮ አገራችን አሁን ካለችበት አሳዛኝ ሁናቴ ላይ አትወድቅም ነበር።

ባሁኑ ወቅት እኛ ውጭ ያለነው ኢትዮጵያውያን ውስጥ ካሉት ምሁራንና ሞያተኞች ጋር በመተባበር አገራችንን በሚመለከቱ ልዩ ልዩ የሆኑ ጥናቶችን ብናከናውን ትልቅ አስተዋጽኦ ይሆን ነበር። ጃፓን፣ ቻይና፣ ህንድ፣ ብራዚል፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ሲንጋፖር፣ ቱርክ፣ ወዘተ የመሳሰሉት አገሮች ካሉበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት በአገራቸው ታሪክ፣ ባህልና ሥልጣኔ ደረጃ ላይ የተመሠረተ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ የኢኮኖሚና የሌሎችም የልማት ዘርፎች የሚስፋፉበትን መንገድ ጥናት ባደረጉ ምሑራን አመራር ነው። እነዚህም Modernizing elites የሚባሉት ናቸው።

ኢትዮጵያ በማንኛውም የልማት መስክ ልትከተል የሚገባትን የዕድገት አቅጣጫ ለመትለምና የማስፈፀሚያ ስልቶችንም ለመቀየስ ብቃት ያላቸው፣ የአዕምሮ በሳልነትና የመንፈስ ጥንካሬ ያላቸው ምሑራንና ሞያተኞች በብዛት አትርፋለች። ኒውዚላንድ፣ አውስትራሊያ፣ ህንድ፣ አውሮፓ፣ ካናዳና አሜሪካ ያሉትን ሞያተኞችና ምሑራን ብቻ መገንዘብ በቂ ነው። አገሪቱ በዚህ የሰው ኃይል ልትጠቀም የምትችለው ለኢትዮጵያ  የሚያስብና ለኢትዮጵያ የቆመ መንግሥት ሥልጣኑን ሲይዝ ብቻ ነው።

ወያኔ አገር ማጥፋቱንና ዝርፊያውን ትቶ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ሥራ ይሠራል ብሎ የሚያምን ኢትዮጵያዊ አይገኝም። ለሶሻሊዝም ነው የምንታገለው የሚሉ ሰዎች ዛሬ የናጠጡ ቱጃሮች ሚሊዬነርና ቢሊዬነር ሆነዋል። ይህም የሚሆነው ሰው በቀን ሁለት ጊዜ እንኳ ለመብላት በተቸገረበት አገር ነው። ከ$30 ቢሊዮን ዶላር በላይ ዕርዳታ ከውጭ ለአገሪቱ ቢሰጥም ገንዘቡ የት እንደደረሰ ሊያወራርዱ አይችሉም። የአገሪቱን በጀት እንኳ አስተካክሎ ሚዛናዊ ለማድረግ ችሎታ እንኳ የላቸውም። ከ20% በላይ የሚሆነው በጀት የሚሸፈነው በውጭ ዕርዳታ ነው። "መሃይም" ብለው የሚጠሩት የቀ.ኃ.ሥ መንግሥት እንኳ አንድ ብር ለበጀት ማሟያ አግኝቶ አያውቅም። ወያኔን አስወግዶ አገሪቱን ለተወሰኑ ዓመታት የሚመራ የሽግግር መንግሥት ማቋቋሙ ተገቢ ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሕዝባዊ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ በድርጅት ያልታቀፉ የአገር ሽማግሌዎች፣ ከአድርባይነት የተቆጠቡና አገሪቱ በጣም የምትፈልጋቸው ምሑሮችና ሞያተኞች የሚካፈሉበት መሆን ይኖርበታል። የታጠቁ

ታጋዮችና እንዲሁም መለዮ ለባሾች ተገቢ ቦታቸውን ይዘው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር አገሪቱን መምራት ይኖርባቸዋል። በብዙ አገሮች የሕዝባዊ ድርጅት አባሎች በፖለቲካ ሥራ አይሳተፉም። ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት አሳሳቢ ሁኔታ ምክንያት ግን የሞያ ማህበራትና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በሥራው የመሳተፍ ጉዳይ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## የሽግግር መንግሥት ከሚሠራቸው አንዳንድ ተግባራት

የሽግግር መንግሥት ማከናወን ያለበትን ተግባር ሁሉ ለማጤን፣ ለመምከር እና መልክ ለማስያዝ የሚያስችል ከልዩ ልዩ የሞያ ዘርፎች የተውጣጣ አንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚሠራ አካል በሕግ ማቋቋም፤

የወያኔን ሕገ-መንግሥት፣ ፓርላማና የክልል ሥርዓት በአዋጅ ሽሮ አዲስ ሕገ-መንግሥት እንዲዘጋጅ ማድረግ፤ ዱሮ የነበሩትን ክፍለ ሃገራት መልሶ በፌደሬሽን የሚዋቀሩበትን መንገድ የሚያጠና አንድ ኮሚሽን ማቋቋም፣ የትምህርት ሥርዓቱ ስለወደቀ የቋንቋ ፖሊሲ ማውጣትና አዲስ የትምህርት ሥርዓት መንደፍ፣ የፖለቲካ እሥረኞችን መፍታት፤ የእርሻ መሬቶችን፣ ደኖችንና ማዕድኖችን የሚያጠናና ለውሳኔ የሚያመች ዘገባ የሚያቀርብ አንድ ኮሚሽን በሕግ እንዲቋቋም ማድረግ፣ ወያኔ ከውጭ መንግሥታትና የግል ድርጅቶች ጋር በኢትዮጵያ ስም የተፈራረማቸውን ውሎች ሁሉ የሚመረምር አንድ ኮሚሽን በሕግ እንዲቋቋም ማድረግ፤ ኢትዮጵያ ተገቢ የሆነ የመከላከያ ኃይል እንዲኖራት ይቻል ዘንድ፣ ከሥራ ገበታቸው የተባረሩና የተፈናቀሉ ሞያተኛ መለዮ ለባሾች ወደሥራ ምድባቸው እንዲመለሱ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ አንድነት በመቆም የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኙትን ቅድሚያ ተሰጥቶ በአገሪቱ መደበኛ የመከላከያ ኃይል አባልነት እንዲሰጣቸው ጥሪ ማቅረብ ይኖርበታል፤ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽንና ከሌሎችም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ስደተኞች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ የመጓጓዣና የመልሶ ማቋቋሚያ የገንዘብ ዕርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርበታል። ከኤርትራ መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተነጋግሮ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት መልክ ማስያዝ፣ ሌሎችም መከናውን ያለባቸው ተግባራት አሉ። ሁሉንም እዚህ መዘረዘሩ ባያስቸግርም ለጊዜው ይኸ ለናሙና ይሁን።

## አካባቢያችን

በአካባቢያችን ያለውን የፖለቲካ ሂደት ብንመለከት ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ታንዛኒያ ሩዋንዳና ብሩንዲ በቅርቡ ፌዴሬሽን ያቋቁማሉ። የሕዝባቸው ብዛት 127 ሚሊዮን ሲሆን፣ በመሬት ስፋት ደግሞ አፍሪካ ውስጥ አራተኛ ይሆናሉ። በዚህም ምክንያት ተደጋጋፊ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ስለሚገኝ ሰፋ ያለ የውስጥ ገበያ አቋቁመው እንዱስትሪን ለመገንባት አመቺ ሁናቴን ይፈጥርላቸዋል ማለት ነው።

ቻድ፣ ሴንትራል አፍሪካን ሪፑብሊክ፣ ጋቦን እና ኢኩዋቶሪያል ጊኒ የጋራ ፓርላማ አቋቁመዋል። የጋራ ፓርላማ ካቋቋሙ ደግሞ የጋራ የመከላከያ ኃይልና የጋራ የውጭ ጉዳይና የዲፕሎማሲ የማቋቋሙ ተግባር ለውይይት ይቀርባሉ ማለት ነው። የፖለቲካ ስምምነት ለኢኮኖሚ ትብብር እና ለጠቅላላው ሂደት መንገዱን ይከፍትላቸዋል ማለት ነው።

በአንፃሩ ግን የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን ሁናቴ ብንዳስስ፣ እንደዚህ ዓይነት አሠራር ፈጽሞ አይታሰብም። የቀረው አፍሪካ ጥሏቸው ሄዷል። እነርሱ ግን በሌላ ዓለም ውስጥ ነው ያሉት። እርስ በእርስ መናቆር፣ የሌለ ችግር መፍጠር፣ ለውጭ መንግሥታት መሣሪያ ሆኖ አገርን ማጥፋት፣ የሕዝቡን ሙብት መጣስ፣ የተማረውን ሕዝብ ማውደም፣ ሕዝቡን በልዩ ልዩ መንገድ እርስ በርስ ማፋጀት፣ ኋላቀርነት፣ ዝርፊያ፣ ስደት፣ ረሃብ፣ ጎስኝነት፣ አምባገነንነት፣ ሌላም፣ ሌላም መጨመር ይቻላል።

በትራንስፖርት በኩል ብንሄድ ለምሳሌ 70% የሚሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓመት ሙሉ የሚያገናኝ መንገድ የለም። የዓለም ባንክ ባደረገው ጥናት መሠረት ብንሄድ አፍሪካ ውስጥ ያለው የትራንስፖርት ዋጋ በ10% እንኳ ቢቀንስ፣ የአፍሪካ አገሮች ንግድ በ85% ሊጨምር ይችል ነበር።

የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ንግድ [የምትሸጠውንና የምትገዛውን] ለማጓጓዝ የሚወጣው ወጭ ብዙዎች አገሮች ከሚከፍሉት በ30% በልጦ ይገኛል። ለተመሳሳይ ተግባር ቻይና የምታወጣው 3% ብቻ ነው። የኢትዮጵያን ሁናቴ

የሚያባብሰው በአገር ውስጥ ያለው የመገናኛ እጦትና ማነስ ሲሆን፣ አገሪቱ ወደብ አልባ መሆኗም ሌላው ተጨማሪ ችግር ነው። መለስ ዜናዊ በተለመደው ቀጣፊነት ተነሳስቶ ኢትዮጵያ ገንዘብ እስካላት ድረስ ወደብ አያስፈልጋትም እያለ እንደሚቀባጥረው ሳይሆን በዓመት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ለአካባቢ አገር ወደቦች ኪራይ መክፈል ቀላል አይደለም። ይህም ወጪ ኢትዮጵያ በዓመት ውጭ የምትሸጠው  ሸቀጣሸቀጥ ጠቅላላ ገቢ የሚያህል ነው። ለዚህ የዕድገት መሰናክል ተገቢ የሆነ መፍትሔ ካልተገኘ የተፈለገውን ያህል ልማት ለማፋጠን ያስቸግራል፤ ሸቀጣ ሸቀጦችን ለውጭ ገበያ በአፋጣኝ መንገድ ለማድረስ ትልቅ ፈተና ይሆናል፤ ከውጭም የሚገባው ሸቀጣ ሸቀጥም ብዙ ክፍያን ይጠይቃል። በአገር ውስጥ የመንገድ ትራንስፖርትን ማስፋፋት፣ የባቡር ሃዲዶችን ኢኮኖሚያዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ መዘርጋትና አፍሪካ ቀንድ ካሉ ወደቦች - ምፅዋ፣ አሰብ፣ ጅቡቲ፣ በርበራ፣ ኪስማዮ፣ ሞቃዲሾና ሞምባሳን ቀረቤታን ማግኘት ያስፈልጋል ማለት ነው።

## ኮንፌዴሬሽንና ፌዴሬሽን

ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ አንዳንድ ኢትዮጵያውያንና፣ ኤርትራውያን ምሑራንና ሞያተኞች ሁለቱ ጎረቤት አገሮች በኮንፌዴሬሽን ጀምረው ወደ ፌዴሬሽን ይሻገሩ ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ  የኮንፌዴሬሽን ሥርዓት ከ ችግር ላይ ችግር ስለሚፈጥርብን በፌዴሬሽን መቀጠል ይሻላል ይላሉ። ድሮውንም ቢሆን ሁለቱ አገሮች የተዋሃዱት በኮንፌዴሬሽን ሳይሆን በፌዴሬሽን ነበር በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ለመሆኑ በሁለቱ የአስተዳደር ሥርዓቶች መካከል ልዩነታቸው የትላይ ነው?

ኮንፌዴሬሽን ልል የሆነ የመንግሥታት መገናኛ ማህበር ነው። መንግሥታት የጋራ ጥቅም የሚያስጠብቁበት ክለብ እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም አባል መንግሥት በፈለገው ጊዜ እራሱን ከአባልነት ለማስወገድ የሚችልበት ሥርዓት ነው። ሥልጣን የሚመነጨው ከመንግሥታት ነው።

ፌዴሬሽንን የወሰድን እንደሆነ፣ መንግሥታት ሥልጣን የሚያገኙት በሕዝብ ፈቃድ ነው። የማዕከላዊው መንግሥት ይሁን የክፍለ ሃገር መንግሥታት የሕዝብን መብት ማክበር ግዴታቸው ነው። የክፍለ ሃገር መንግሥታት ሕዝቡን ሲበድሉ፣ ሕዝቡ አቤቱታውን ለማዕከላዊው መንግሥት ማቅረብ ይችላል። በደሉ የመነጨው ከማዕከላዊው መንግሥት ከሆነ ሕዝቡ አቤቱታውን ለክፍለ ሃገር መንግሥታት ማቅረብ ይችላል። ሕዝቡ ማዕከላዊውን መንግሥትም ይሁን የክፍለ ሃገር መንግሥታት በምርጫ ከሥልጣን ለማውረድና ለማሰናበት ይችላል።

በኮንፌዴሬሽን አባሎች ከልዩ ልዩ መንግሥታት መዋዋል ይችላሉ። በፌዴሬሽን ግን የዚህ ዓይነት ሥልጣን የማዕከላዊው መንግሥት ሥልጣን ነው። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የዲፕሎማሲ፣ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የውጭ ንግድ፣ የብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕቅድ ሥራ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመንገድና የባቡር ሃዲድ ሥራና አስተዳደር፣ የማዕከላዊ ባንክና የመገበያ ገንዘብ አሠራር፣ የማዕድን ሃብት፣ የደኖች አጠባበቅ፣ የወንዞችና የግድብ ሥራ፣ የወደቦች አስተዳደር ወዘተ ይኸ ሁሉ ተዳምሮ የፌደራል መንግሥት ኃላፊነት ነው።

ኤርትራና ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋቸው ሰላም፣ ልማት፣ ዕድገት፣ ብልጽግና ከሆነ ይህ ሊጠናቀቅ የሚችለው በፌደሬሽን እንጂ በበኮንፌዴሬሽን ሊሆን አይችልም።  በተጨማሪ ኤርትራ ነፃነቷን ስትቀዳጅ በሁለቱ ጎረቤት አገሮች መካከል ተንጠልጥለው ያሉ እስከአሁን ድረስ መፍትሔ ያላገኙ ችግሮች እንዳሉ ነው። ለምሳሌ ያህል የወሰን ጉዳይ፣ የእሥረኞች ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ የባህር ኃይል መርከቦች፣ የቤንዚን ማጣሪያው ባለቤትነት፣ የወደቦቹ ጉዳይ፣ ኤርትራ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን መብት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ኤርትራውያን መብት፣ ወዘተ ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች ኮንፌዴሬሽን መፍትሔ ሊሰጥ አይችልም። እንዳውም ከችግሩ ላይ ችግር ነው የሚጨምረው። ፌደሬሽን ግን ለተጠቀሱት ችግሮች ሁሉ መፍትሔ ይሰጣል።

በኢኮኖሚ በኩል የሄድን እንደሆነ ደግሞ ኮንፌዴሬሽን ብዙ ችግር ይፈጥራል። አንዱ አገር ከሌላው ጋር የንግድ ልውውጥ ለማድረግ ቢፈለግ ክፍያው በውጭ ምንዛሪ መሆን ይኖርበታል። እነኝህ አገሮች ደግሞ የውጭ ምንዛሪ በማግኘቱ በኩል ብዙ ችግር አለባቸው። በፌዴሬሽን የሄድን እንደሆነ ግን ሁለቱም አገሮች የሚገበያዩበት በአንድ አይነት የመገበያያ ገንዘብ ስለሆነ የክፍያው ጉዳይ መልኩን ይለውጣል።

## የኢትዮጵያና የኤርትራ ፌዴሬሽን

ሁለቱ አገሮች በፌዴሬሽን ከመዋቀራቸው በፊት በሁለቱም አገሮች መከናወን ያለባቸው ብዙ ተግባራት አሉ። ለምሳሌ ያህል የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ በሥልጣን ላይ የሚኖረውን መንግሥት አግባብ ባለው መንገድ የመንቀፍ መብት የማክበር ጉዳይ፣ የባለሥልጣኖቹ ለሕግ ተገዥነትና የህግ የበላይነትን መቀበል፣ የፍርድ ቤቱ ነፃ መሆን፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት ሜዲያውን የመጠቀም መብት እና ፕሮግራማቸውን ለሕዝብ አቅርበው በሕዝብ ፊት ተገምተው መመረጥ፣ የጋዜጦቹ ሚዛናዊነት፣ ክፍላተ ሃገራት ራሳቸውን የማስተዳደር መብት፣ የክፍለ ሃገር፣ አውራጃና ወረዳ አስተዳዳሪዎች በሕዝብ የመመረጥ መብት፣ ከተማዎቹ በሕዝብ በተመረጡ ከንቲባዎች የመስተዳደር መብት፣ ወዘተ

የሚቋቋሙት ጥንታዊ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገራት በመሬት ስፋት፣ በሕዝብ ብዛትና በተፍጥሮ ሀብት ተመጣጣኝ ስለሚሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋመው ፌደሬሽን ቋሚነት ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ ያህል ወሎ 71,200$^2$ ኪ.ሜ ሲሆን ጐንደር 74,200$^2$ ኪ.ሜ፣ ወሎ 79,400$^2$ ኪ.ሜ ሲሆን ትግራይ 65,900$^2$ ኪ.ሜ ነበር። አሁን ግን በመሪዎቹ የተስፋፊነት ዓላማ የትግራይ ስፋት 102,000$^2$ ኪ.ሜ ሆኗል። ይህም ሊሆን የቻለው የጐንደርንና የወሎን ሕዝብ አባረው መሬቱን ቀምተው በቅኝ ግዛትነት በያዙት መሬት ምክንያት ነው። ይኸ ግን በወሎና በጐንደር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀባይነት የለውም።

በሁለቱ አገሮች ውስጥ የሚደረገው ተገቢ የሆነ ለውጥ የኤርትራንና የኢትዮጵያን በፌደሬሽን ማዋቀር አስተማማኝ እንዲሆን ያደርገዋል። ካለፈው ችግር ብዙ ትምህርት አግኝተናል። ለችግሩም መፍትሔ አለን።

አንዳንድ አገሮች በኢኮኖሚ ውህደት ይጀምሩና ወደ ፖለቲካ ውህደት ይሄዳሉ። የኢትዮጵያና የኤርትራ ችግር የኢኮኖሚ ውህደት ሳይሆን የአስተዳደርና የፖለቲካ ፍልስፍና አለመጣጣም ነበር። አሁንም ቢሆን በኢኮኖሚ ውህደት መጀመሩ ትርጉም የለውም። በአንድ የጋራ ገበያ ውስጥ የነበረ አገር ስለነበረ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ መሆን የለበትም። በፖለቲካ ውህደት መጀመር ያለባቸው ፀጥታን ለማስጠበቅ፣ በአካባቢው ከተነሳው ብጥብጥና አሳሳቢ ግፊት ሕዝቡን ለማዳን፣ ልማትና ዕድገትን ለማፋጠን፣ ለሁለቱ አገሮች ዕድገት በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ፕሮጀክቶች አብረው በትብብር መልክ ለማስያዝ ነው።

የተባለው ፌደሬሽን የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን ለማዋሃድ ለምናደርገው ጥረት መሠረትና ምሰሶ እንዲሆን ነው። ይህም ማለት ጅቡቲ፣ ሶማሊላንድ፣ ፑንትላንድ፣ እንዲሁም የቀረው ሶማልያ ደረጃ በደረጃ የፌደሬሽን አባል እንዲሆኑ ኢትዮጵያና ኤርትራ የሚያቋቁሙት ፌደሬሽን ድልድይ ይሆናል ማለት ነው።

የኤርትራ የግዛት አንድነት፣ ፓርላማ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ የውስጥ አስተዳደር ነፃነቷ ሁሉ የተከበረ ይሆናል ማለት ነው። የፌደሬሽኑ ፓርላማ አስመራ፣ መቀሌ፣ ጐንደር፣ ጅማ፣ አዋሳ፣ ሐረር ወዘተ ሊሆን ይችላል። አንድ ቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሞ እነኝህ ከተሞች ምክር ቤቱን ለማስተናገድ ያላቸውን አቅም አጥንቶ ሪፖርት ማቅረብ ይችላል። በፌደሬሽኑ ሕዝብ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የመማር፣ የመሥራት፣ የማረስ፣ ንግድ የማቋቋም፣ ፋብሪካ የመክፈትና በሚኖርበት ቦታ የመምረጥና የመመረጥ መብቱ የተከበረ ይሆናል።

በወያኔ ዕርዳታ የተወሰኑ የኤርትራ መንግሥት ፖለቲካ ተቃዋሚዎች መቀሌ ከተማ ቢሮ ከፍተዋል። የትግላቸው መርሆ "የኤርትራ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ዕራስንበራስ የማስተዳደር መብት እስከ መገንጠል ድረስ" የሚል ነው። አፋር፣ ሳሆ፣ ቢለን፣ ትግረኛ ቋንቋ የሚናገረው ሕዝብ ወዘተ ወኪሎች ኤርትራን ነፃ እናወጣለን ብለው የተደራጁትን ፓርቲዎች ይደግፋሉ ይባላል። እንደዚህ ያለ ሁናቴ ትግሉን ወደ ሌላ አቅጣጫ እንደሚያመራው ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይደለም። ወያኔ ገንዘብ፣ ሃብት፣ "ብልሃት"፣ "ዕውቀትና" መሣሪያ ስላለኝ ኤርትራኖችንም በቁጥጥር ሥር ላስገባችሁ ያለ ይመስለኛል። እኛ ግን ኤርትራ ኤርትራ እንደሆነች፣ ኢትዮጵያም ኢትዮጵያ እንደሆነች በፌደሬሽን ይዋቀሩ ነው የምንለው። ይህ "The Ethiopianization of Eritrea" ብለን የምንሰይመው ሥራ ወያኔ ከውጭ የተሰጠው ትዕዛዝ ነው። የኤርትራና ኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ተጠብቆ ወደ ፌደሬሽን መሄዱን ግን እኛ የምንደግፈው ነው።




For any comments or questions you can reach the author at: *kendied@hsu.edu*